# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል የተሰጠ

# የነገረ ማርያም ኮርስ




**አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ**

**(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)**


**ሐምሌ ፯፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም**

## ነገረ ማርያም

ስለእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሕይወት፣ ስለቅድስናዋ፣ ስለንጽሕናዋ፣ ስለዘለዓለማዊ ድንግልናዋ እና በነገረ ድኅነት ስላላት ሚና የምንማማርበት የነገረ መለኮት ትምህርት ነገረ ማርያም (Mariology) ይባላል፡፡

### ነገረ ማርያምን የመማር ጥቅም

- ✓ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገውን የማዳን ሥራ በትክክል ለመረዳት
- ✓ ነገረ ክርስቶስን ለመረዳት
- ✓ ኦርቶዶክሳዊ ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት ለማወቅ

### ማርያም ማለት ምን ማለት ነው?

- ➢ ማርያም ማለት እመ ብዙኃን (የብዙዎች እናት) ማለት ነው፡፡
- ➢ መርሕ ለመንግሥተ ሰማያት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ምክንያተ ድኅነት በመሆኗ ነው፡፡
- ➢ ጸጋ ወሀብት ማለት ነው፡፡ ይኸውም ለጊዜው ለእናት ለአባቷ ልጅ በመሆኗ ሲሆን ፍጻሜው ለምእመናን በምልጃዋ የምትረዳ በመሆኗ ነው፡፡
- ➢ ፍጽምተ ሥጋ ወነፍስ ማለት ነው፡፡ ይኸውም በድንግልና ጸንታ የኖረች፣ ከነቢብ፣ ከገቢር፣ ከኀልዮ ኃጢአት የራቀች፤ ምንም ዓይነት እንከን የሌለባት ንጽሕተ ንጹሓን ማለት ነው፡፡
- ➢ መልዕልተ ፍጡራን መትሕተ ፈጣሪ ማለት ነው፡፡
- ➢ ታኦዶኮስ (ቴዎቶኮስ) ማለት ነው፡፡ ይኸውም ወልደ እግዚአብሔርን በሥጋ የወለደች ማለት ነው፡፡
- ➢ እግዝእተ ብዙኃን (የብዙዎች እመቤት) ማለት ነው፡፡ እመቤት ማለት በቤተሰብ መካከል አስተዳዳሪና ኀላፊ የሆነች ታላቅ ሴት ማለት ነው፡፡ ድንግል ማርያምም በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖች ሁሉ አንድ ቤተሰብ በመሆናቸው የክርስቲያኖች ሁሉ እመቤት ናት ማለት ነው፡፡
- ➢ ተለዓኪተ እግዚአብሔር ወሰብእ ማለት ነው፡፡ ይኸውም ለአምላክ ሰው የመሆኑ ምክንያት ለሰው ደግሞ የመዳኑ ምክንያት በመሆኗ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ ወደ ሰው የሰውን ልመና ወደ እግዚአብሔር የምታደርስ በመሆኗ ነው፡፡

### ድንግል ማርያም

- ❖ ቅድስት ናት፡- ቅድስት ማለት ከርኵሰት ከበደል የተለየች፣ በሃይማኖት በምግባር በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደች ማለት ነው፡፡ ድንግል ማርያም በሕይወቷ ከሰው ልጆች ሁሉ ተለይታ የከበረች በመሆኗ ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች፡፡
- ❖ ንጽሕት ናት፡- ድንግል ማርያም በንጽሕና ከመላእክት ትበልጣለች መባሏ መላእክት ባይበድሉ ፍትወተ ሥጋ በማይስማማው ባሕርይ ስለተፈጠሩ በንጹሕ ዓለም ሆነው ነው፡፡ ድንግል ማርያም ግን ድካም በሚስማማው ፍትወት በሚጥለው ሥጋዊ ደማዊነት ባለበት በሰው ተፈጥሮ ሳለች በመርገም በተያዘ ትውልድ መካከል ሳለች ንጽሕናን ይዛ በመገኘቷ ከመላእክት ትበልጣለች ተብሏል፡፡ ንጽሕተ ንጹሓን መባሏ ስለዚህ ነው፡፡
- ❖ ቡርክት ናት፡- ድንግል ማርያም ከሴቶች ሁሉ ተለይታ የተባረከች ተብላለች፡፡ ከሰው ልጆች ሁሉ ንጽሕት ሆና ቢያገኛት ወልደ እግዚአብሔር ለእናትነት መርጧታል፡፡ እግዚአብሔር

ሰዎችን ፍጻሜያቸውን አስቀድሞ አውቆ ይመርጣል እንጂ ወስኖ መርጦ የፈጠረው ሰው የለም፡፡ ድንግል ማርያምን ለመመረጥ ያበቃት ንጽሕናዋ ነው፡፡

- ንጽሐ ጠባይዕ ያላደፈባት ናት፡፡ በአዳም በደል ምክንያት ሰው ሁሉ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የደረሰበት ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ድንግል ማርያምን ግን ራሱ እግዚአብሔር ከማሕፀን ጀምሮ የባሕርይ ጉስቁልና እንዳይደርስባት ጠብቋታል፡፡ በወንጌል እንደተገለጸው ጌታን መድኀኒቴ ማለቷም መርገም ወደ እርሷ እንዳይደርስ ከማሕፀን ጀምሮ ስለጠበቃት ነው፡፡ ስለዚህ ወልደ እግዚአብሔር ንጽሕት ሆና ቢያገኛት ከእርሷ ሰው ሆነ እንጂ መርገም ኑሮባት አንጽቶ ከእርሷ ሰው ሆነ አይባልም፡፡ “ጌታችን የዚህችን ድንግል ንጹሕ ሥጋዋን ንጽሕት ነፍሷን ባገኘ ጊዜ ነፍስ ያለችውን ሥጋ ሊዋሐደው ፈጠረ” እንዲል (ሃይ.አበ.66፥14)፡፡ በተጨማሪም ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ ድንግል በኀሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ” ይላል (ሃይ.አበ.53፥22)፡፡
- በእሾህ መካከል ያበበች አበባ ናት (ቅዱስ ያሬድ)፡፡ ድንግል ማርያም በአዳም አካል እንደ ዕንቍ ታበራ ነበር መባሉም ሐሳቡ ተመሳሳይ ነው፡፡ ይኸውም ድንግል ማርያም የአዳም መርገም ያልደረሰባት ንጽሕት መሆኗን ለመግለጽ ነው፡፡ የጽጌረዳ አበባ እሾህ ካለው ግንድ ቢገኝም አበባው ግን እሾህ የሌለበት፣ መዓዛው ያማረ እንደሆነ ሁሉ ድንግል ማርያምም ምንም እንኳ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ከነበረባቸው ሰዎች ብትገኝም እርሷ ግን መርገም የሌለባት ንጽሕት ናት፡፡

### የእመቤታችን ሐረገ ትውልድ

ድንግል ማርያም ከነገደ ይሁዳና ከነገደ ሌዊ ተወልዳለች፡፡ የመጨረሻዎቹ ሰባቱ አያቶቿ (ቴክታ[ሴ] + ጸጥሪቃ [ወ]፣ ሄኤሜን፣ ዴርዴን፣ ቶና፣ ሲካር፣ ሴትና፣ ሔርሜላ፣ ሐና፣ ድንግል ማርያም፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይላል፡፡ ይህ በሴት አያቶቿ ሲቆጠር ነው፡፡

## የዮሴፍና የድንግል ማርያም ዝምድና




የጌታን የትውልድ ሐረግ ወንጌላዊው ማቴዎስ በዮሴፍ በኩል የቆጠረው በአይሁድ ልማድ ትውልደ አበው የሚቆጠር በወንድ በኩል ስለሆነ ነው፡፡ ድንግል ማርያም የዮሴፍ እጮኛ መባሏ ዘመዷ በመሆኑ ከአይሁድ፣ ከክፉ ሰዎች እንዲጠብቃት በአደራ ስለሰጠችው ነው፡፡ ይህ እጮኝነት የጥበቃ እጮኝነት እንጂ የጋብቻ እጮኝነት አይደለም፡፡

## ከድንግል ማርያም ሕይወት ምን እንማራለን

- እምነት (ይኩነኒ) ማለቷ
- ትሕትና፣ ምስጢራዊነቷ (ይህንን ሁሉ በልቧ ትጠብቀው ነበር እንዲል)
- ለፍጡራን ማዘንን (ለተጠማ ውሻ በማጠጣቷና በቃና ሰርግ ለዶኪማስ መራራቷ)
- በኀልዮ፣ በገቢር፣ በነቢብ አለመበደል

## የእመቤታችን ዘለዓለማዊ ድንግልና

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጊዜ ፀኒስ፣ ቅድመ ፀኒስ፣ ድኅረ ፀኒስ፣ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ ድንግል ናት፡፡ መልአኩ ዮሴፍን ከእርሷ የሚወለደው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህ ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ ብሎታል፡፡ ዮሴፍ የፈራው ለምንድን ነው? የታጨችው ለሚስትነት ቢሆን ኖሮ በፀነሰች ጊዜ አይፈራም ነበር፡፡ ዮሴፍ የፈራበት ምክንያት ያለሕግ ፀነሰች ብለው ይገድሉብኛል ብሎ ነው፡፡ ድንግልና ማለት ከዝሙት፣ ክፉ ሐሳብን ከማሰብ መታቀብ ማለት ነው፡፡ የበኵር ልጇን እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም የሚለውም ከወለደች በኋላ በግብር አወቃት ማለት አይደለም፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንደገለጸው በልደት ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች የአምላክ እናት መሆኗን እስኪዳ አላወቀም ነበር፡፡ በልደት ጊዜ ግን የሰብአ ሰገልን መምጣት፣ የኮከብ በተለየ መልኩ መሔድን፣ የመላእክትን ምስጋና፣ የእረኞችን ምስጋና አይቶ የአምላክ እናት መሆኗን አወቀ ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ድንግል ማርያም ጌታን በፀነሰች ጊዜ መልኳ ይለዋወጥ ስለነበር በቋሚ መልኳ አያውቃትም ነበር፡፡ ከወለደች በኋላ ግን መልኳ ስላልተለዋወጠ አወቃት ማለት ነው፡፡

## ድንግል ማርያም በትንቢተ ነቢያት

የድንግል ማርያምን ዘለዓለማዊ ድንግልና ለመግለጽ ነቢዩ ቅዱስ ኢሳይያስ "እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች" ብሎ ተናግሯል (ኢሳ.7፥14)፡፡ በሌላ ክፍልም ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ የነጻች መሆኗን ለመግለጽ "ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል" ተብላለች (መዝ.45፥4)፡፡ ቅዱስ ዳዊት ቀጥሎ "ደብረ ጽዮን ዘአፍቀረ ሐነፀ መቅደሶ በአርያም ወሣረራ ውስተ ምድር ዘለዓለም" ብሏል (መዝ.77፥68)፡፡ የጽዮን ተራራ የተባለች ድንግል ማርያም ናት፡፡ መቅደስ የተባለችም ራሷ ናት፡፡ እንደ አርያም ሠራ መባሉ አርያም ሥሉስ ቅዱስ የሚገለጡበት የተለየ የክብር ቦታ እንደሆነ ሁሉ በድንግል ማርያምም አብ ለአጽንዖ፣ ወልድ ለተሰብኦ፣ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ አድረውባታልና፡፡ "እስመ ኀረያ እግዚአብሔር ለጽዮን ወአብደራ ከመ ትኩኖ ማኅደሮ፡፡ ዛቲ ይእቲ ምዕራፍየ ለዓለም" እንዲል (መዝ.131፥13)፡፡ የድንግል ማርያም አያቶቿ፣ ቅድመ አያቶቿ ቅዱሳን መሆናቸውን ለመግለጽም ቅዱስ ዳዊት "መሠረቶቿ የተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ብሏል፡፡

## የድንግል ማርያም ምሳሌዎች

አበው ደግ የሆነውን ነገር ሁሉ እየፈለጉ የክርስቶስና የድንግል ማርያም ምሳሌ እያሉ ይመስሉታል፡፡ ቅዱሳን ነቢያት በዘመናቸው ልዩ ልዩ ትንቢቶችን ቢናገሩም የኋላ ሊቃውንት የምስጢሩን ቀናነት አይተው ምሳሌ መስለዋል፡፡ ከምሳሌዎቹ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ ሁሉም ግን ምሳሌ ዘየሐጽጽ (ጉድለት ያለባቸው ምሳሌዎች) ናቸው እንጂ ሁለንተናቸው ድንግል ማርያምን ይመስላል ማለት አይደለም፡፡

| ምሳሌ | ጥቅስ | ሐተታ |
| --- | --- | --- |
| የማክሰኞ እርሻ | ዘፍ.1፥11 | የሥነ ፍጥረቷ የማክሰኞ እርሻ ዘር ሳይዘራባት እንዳበቀለች ድንግል ማርያምም ያለ ወንድ ዘር ጌታን ወልዳዋለችና። |
| የአቤል ደግነት | ዘፍ.4፥4 | ጌታ የአቤልን መሥዋዕት የተቀበለው ደግነቱን አይቶ ነው። ድንግል ማርያምንም ለእናትነት የመረጣት ደግነቷን አይቶ ነውና። |
| የኖኅ መርከብ | ዘፍ.6፥4 | ኖኅ የጌታ ምሳሌ ነው። በሌላ መልኩ ኖኅ በመርከቧ ምክንያት እንደዳነ ድንግል ማርያምም ጌታን በመውለዷ ምክንያት ሰው እንደዳነ ያመለክታል። |
| ሰላማዊት ርግብ | ዘፍ.8፥11 | የወይራ ቅጠል የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ርግብ የወይራ ቅጠልን ይዛ መጥታ የማየ አይኅን መጉደል እንዳበሰረች ድንግል ማርያምም ጌታን በመውለዷ በጌታ ፍዳ መጥፋቱን ያመለክታል። |
| ቀስተ ደመና | ዘፍ.9፥8-15 | ቀስተ ደመና የይቅርታ ምልክት እንደሆነ ድንግል ማርያምም አምላክን በመውለዷ የመዳናችን ምልክት ናትና (ኢሳ.7፥14)። |
| ዕፀ ሳቤቅ | ዘፍ.22፥9-13 | ይስሐቅ የአዳምና የዘሩ፣ በይስሐቅ ፈንታ የታረደው በግ የክርስቶስ፣ በጉ የመጣበተ ዕፀ ሳቤቅ የድንግል ማርያም ምሳሌ ነው። |
| የያዕቆብ መሰላል | ዘፍ.28፥10-20 | በመሰላል ከላይ ወደ ታች ከታች ወደ ላይ እንደ ሚወጡበት ሁሉ ድንግል ማርያምም ለቃል ርደት ለሥጋ ዕርገት ምክንያት ናትና። |
| ዕፀ ጳጦስ | ዘፀ.3፥1-6 | ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ሁሉ ድንግል ማርያምም እሳተ መለኮትን ስትፀንስ አላቃጠላትምና |
| ታቦተ ሙሴ | ዘፀ.25፥10-22 | ጽላት የክርስቶስ ታቦት የድንግል ማርያም ምሳሌ |
| በትረ አሮን | ዘኍ.17፥8-11 | የአሮን በትር ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ አፍርታ እንደተገኘች ድንግል ማርያምም ያለወንድ ዘር ጌታን ፀንሳ ወልዳልናለችና። |
| የጌዴዎን ፀምር | መሳ.5፥36-40 | ፀምር የእመቤታችን፣ ጠል የጌታ ምሳሌ ነው። ጠል ተለይቶ በፀምር እንደወረደ ጌታም ከሴቶች ሁሉ በተለየ በድንግል ማሕፀን ተወስኗልና። |
| የኤልያስ ደመና | 1ኛ ነገ.18፥41 | ትንሿ ደመና የድንግል ማርያም፣ ዝናም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶሰ ምሳሌ |
| የኤልያስ መሶበ ወርቅ | 1ኛ ነገ.19፥1-8 | ኤልያስ የአዳም፣ መሶብ የእመቤታችን፣ ወርቅ የንጽሕናዋ፣ ምግቡ የክርስቶስ ምሳሌ |
| የኤልሳዕ ማሰሮ | 2ኛ ነገ.2፥19 | አዲስ ማሰሮ የእመቤታችን፣ ጨው የክርስቶስ፣ የውሃው መምረር የመርገም ምሳሌ ነው። |
| ከፍ ያለች ዙፋን | ኢሳ.6፥1 | ረጅምና ከፍ ያለ ዙፋን የእመቤታችን፣ ጌታ በላይዋ ተቀመጠ መባሉ በማሕፀኗ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የመቀመጡ ምሳሌ |
| የእሴይ በትር | ኢሳ.11፥1 | በትር የድንግል ማርያም፣ አበባ የክርስቶስ ምሳሌ |

| | | |
|---|---|---|
| የሕዝቅኤል ደጅ | ሕዝ.44፥1 | በዚህ ደጃፍ የኀያላን አምላክ ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት እንደወጣ ሁሉ ጌታም ከድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወልዷልና፡፡ የተዘጋ በር የድንግልናዋ ምሳሌ፡፡ |
| ታላቂቱ ተራራ | ዳን.2፥31-35 | ከተራራው ድንጋይ ወርዶ ጣዖቱን እንዳፈረሰው ሁሉ ከድንግል ማርያምም ጌታ ተወልዶ ፍዳን አጥፍቷልና ድንጋይ የክርስቶስ ምሳሌ (1ኛ ቆሮ.10፥4) |
| ቤተልሔም | ሚክ.5፥2 | ልሔም የክርስቶስ ምሳሌ |
| ኤፍራታ | | ኤፍራታ ማለት ጸዋሪተ ፍሬ ማለት ነው፡፡ ፍሬ የጌታ ምሳሌ ነው፡፡ |
| የተቀደሰች ምድር | ዘፀ.3፥6 | ምድር ሁሉ ተረግማ ሳለ ሙሴ ጫማህን አውልቅ የተባለባት ምድር ግን ቅድስት ነበረች፡፡ ዓለም በመርገመ ሥጋ ወነፍስ ተይዞ ሳለ መርገም ያልደረሰባት በመሆኗ ድንግል ማርያም የተቀደሰች ምድር ትባላለች፡፡ |
| ለእስራኤል ውሃ ያፈለቀች ድንጋይ | ዘፀ.17፥6<br>ኢሳ.48፥21 | ከድንጋይ የፈለቀው ውሃ የሕይወት ውሃ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ |
| ከሞተ አንበሳ የተገኘች የማር ወለላ | መሳ.14፥6-9 | መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ ካለባቸው ሰዎች ተወልዳ እርሷ ግን መርገም የሌለባት በመሆኗ የማር ወለላ ተብላለች፡፡ |
| የበረሃ የሱፍ አበባ | መሓ.2፥1 | አበባው የድንግል ማርያም፣ መዓዛው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ፡፡ |
| ማርና ወተትን የምታፈስዋ መልካሚቱ ምድር የምድር ጌጥ | ዘኍ.14፥7<br>ዘፀ.3፥7<br>ሕዝ.20፥15 | ማርነ ወተት የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ ተድላ ደስታም የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ |
| ቤቴል | ዘፍ.30፥13 | ቤቴል ማለት የአምላክ ቤት ማለት ነው፡፡ ድንግል ማርያም ጌታን ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀኗ ወስናዋለችና ቤቴል ትባላለች፡፡ |
| ንጹሕ የሽቱ ዕቃ | ዘፀ.30፥34 | ሽቱው የክርስቶስ ምሳሌ |
| ንጹሕ አዳራሽ | ሚል.3፥1 | ጌታ ወደዚች አዳራሽ እንደሚገባ መናገሩ ከድንግል ማርያም እንደሚወለድ ያመለክታል |
| ደብረ ፋራን | ዕን.3፥3 | እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ሰው ሆኖ እንደሚመጣ ያመለክታል |
| ፈዋሲተ ቍስሉ ለናሆም | ናሆ.3፥19 | ዓለም ሁሉ በቍስለ ኃጢአት ተይዞ ሲኖር በደል የሌለባት ሆና መድኀኒት ጌታን ስለወለደችልን |
| የወርቅ መቅረዝ | ዘፀ.25፥31 | የፈትል ማስቀመጫው የማሕፀኗ፣ ፈትል የትስብእት እሳት የመለኮት፣ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ |
| አትሮንስ ሰሎሞን | መሓ.3፥11 | ሰሎሞን የጌታ ምሳሌ ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| ገነት ዕፁት አዘቅት ኅትምት | መሓ.4፥12 | የታጠረች አፀድ ከተከሉባት መልካም ተክል በቀር ሌላ እንደማይገባባት በድንግል ማርያም ኅሊናም መልካም ሐሳብ ብቻ መኖሩን ያመለክታል፡፡ የታተመች ውሃ በውስጧ ካለው ውሃ በቀር ሌላ እንደማይገኝ ድንግል ማርያምም ክርስቶስን ብቻ መፅነሷን ያመለክታል፡፡ ገነት የድንግል ማርያም፣ ተክል የጌታ ምሳሌ፡፡ ውሃ የጌታ፣ የታታመች ጉድጓድ የድንግል ማርያም ምሳሌ |
| በሰማይ የታየች ዙፋን | ሕዝ.1፥26 | በዙፋኑ ሰው ተቀምጦ እንደነበር ሰው የተባለ ክርስቶስ በድንግል ማሕፀን መኖሩን ያመለክታል፡፡ |
| ዐፅቀ አቤሜሌክ | ባሮ.3፥1 | ዐፅቀ አቤሜሌክ ለ66 ዓመታት ሳትጠወልግ እንደኖረች ድንግል ማርያምም በ66ኛው ትውልድ መርገመ ሥጋ ወነፍስ ሳይኖርባት ተገኝታለችና፡፡ |
| ደብተራ ኦሪት | ዘፀ.30፥26 | ደብተራ ኦሪት በጸጋ ማኅደረ እግዚአብሔር እንደ ነበረች ድንግል ማርያምም የሥላሴ ማደሪያ ሆናለችና |
| መቅደሰ ሰሎሞን | 1ኛ ዜና 22፥19 | ›› ›› ›› ›› ›› ›› ›› ›› |
| ቅድስተ ቅዱሳን | ዘፀ.30፥10 | ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚገባባት ናት ድንግል ማርያምም ሊቀ ካህናት ክርስቶስን ወልዳልናለችና ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች፡፡ |
| ዳንኤል የነበረባት ጉድጓድ | ዳን.14፥38 | ነቢዩ ዕንባቆም ድንጋዩን ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት እንደወጣ ሁሉ ጌታም የድንግል ማርያምን ማሕተመ ድንግልናዋን ሳይለውጥ ተፀንሶ ተወልዷል፡፡ |
| የሕይወት ዛፍ | ዘፍ.2፥9 | ጌታ የፍሬ ሕይወት ምሳሌ |
| በወርቅ የተለበጠች ማዕጠንት | ዘፀ.40፥5 | ማዕጠንቱ የተሠራበት የማይነቅዝ እንጨት ድንግል ማርያም መርገም የሌለባት ለመሆኑ ምሳሌ፣ ወርቅ የንጽሕናዋ ምሳሌ፡፡ ዕጣን የትስብእት፣ ፍሕም የመለኮት ምሳሌ |
| መሶበ ወርቅ | ዕብ.9፥4 | በመሶቡ ያለው መና የክርስቶስ ምሳሌ |
| ጽላት ዘሙሴ | ዘፀ.24፥12 | በጽላቱ የተጻፈው ቃል የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ |
| ሀገረ እግዚአብሔር | መዝ.45፥4 | ወንዝ የተባለ ቅዱስ ገብርኤል ነው |
| የዳዊት መሰንቆ | 1ኛ ሳሙ.16፥23 | መሰንቆው ሲመታ ድውያን ይፈወሱ ነበር፡፡ የመሰንቆው ድምፅ የጌታ ምሳሌ |
| ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን | ዘፀ.39፥26 | የዚህን የጸናጽሉን ድምፅ ሰምተው በሽተኞች ይፈወሱ እንደነበረ ጌታም ዓለምን አድኗልና፡፡ የጸናጽሉ ድምፅ የጌታ ምሳሌ |
| ሐውልተ ስምዕ ዘኢያሱ | ኢያ.7፥26-27 | ይህ ሐውልት ሲተከል መቅሠፍተ እግዚአብሔር እንደራቀ ድንግል ማርያምም በምልጃዋ መዓትን ታርቃለችና፡፡ ይህ ሐውልት ሦስት ገጽ እንደነበረው ድንግል ማርያምም ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ወሊድ በሦስቱም ድንግል ናትና |

| | | |
|---|---|---|
| ዕራቃ ደመና | ተረ.ቁር.18፥6 | ዕራቃ ደመና ማለት ነፋስ ያላጠቆራት ደመና ማለት ነው። ድንግል ማርያምም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የለባትምና ዕራቃ ደመና ትባላለች |
| ሙዳየ አሚን | ቅዱስ ኤፍሬም | አሚን የጌታ ምሳሌ |
| መዝገበ ዮሴፍ | ቅዱስ ኤፍሬም | ዮሴፍ የተቀለፈች ሳጥን ገዝቶ ውስጧን ሲመለከት ዕንቊ አግኝቶባታል። ዕንቊ የጌታ ምሳሌ |
| ንጹሕ የሰርግ ቤት | ›› ›› ›› ›› | በሰርግ ቤት የሙሽሪትና የሙሽራው ዘመዶች አንድ እንደሚሆኑ በድንግል ማርያም ማሕፀንም ቃልና ሥጋ በተዋሕዶ አንድ ሆነዋልና። |
| ኢየሩሳሌም | ›› ›› ›› ›› | ኢየሩሳሌም ማለት ሀገረ ሰላም ማለት ነው። ሰላም የክርስቶስ ምሳሌ |
| ዳግሚት ሰማይ | ›› ›› ›› ›› | ሰማይ ልዑል እንደሆነ ድንግልም ልዕልት ናትና |
| የመላእክት ደስታቸው | ›› ›› ›› ›› | መላእክት ጌታን ሰው ሆኖ ማየት ይፈልጉ ነበር። ከእርሷ ተወልዶ አይተውታልና ደስ ብሏቸዋል። እንዲሁ በቅድስናዋ ይደሰቱ ነበርና |
| የነቢያት ዜናቸው | ›› ›› ›› ›› | ስለእርሷና ስለልጇ ትንቢት ተናግረዋልና |
| የሕያዋን ሁሉ እናት | ›› ›› ›› ›› | ሕያዋን በልጇ አምነው ተጠምቀው ይኖራሉ። እርሱን የወለደች እርሷ ናትና። |
| ደብር ነባቢት፣ ገነት ነባቢት | ›› ›› ›› ›› | በደብረ ሲና ሙሴ ከጌታ፣ በገነት አዳም ከጌታ ጋር ተነጋግረዋል። ድንግል ማርያምን ግን ራሱ ተናግሯታልና ነባቢት ብሏታል። |
| እናትና አገልጋይ | ›› ›› ›› ›› | በተፈጥሮ ፈጥሯታልና አገልጋይ ስትባል በሥጋ ወልዳዋለችና እናቱ ተብላለች። |
| የደናግል መመኪያ | ›› ›› ›› ›› | ሔዋን ከአዳም ብትገኝ ጌታ ከድንግል ማርያም ተወልዷልና። ወንዶች ሴቶችን በእናንተ ምክንያት ከገነት ወጣን ሲሏቸው ሴቶች ደግሞ በእኛ ምክንያትስ ወደ በለጠችዋ መንግሥተ ሰማያት ገባችሁ አይደል እያሉ ይመኩባታልና። |
| የብርሃን እናት | ›› ›› ›› ›› | ብርሃን ጌታን ወልዳለችና |
| ሰአሊተ ምሕረት | ›› ›› ›› ›› | ለሰው ሁሉ ምሕረትን ትለምናለችና |
| ምልእተ ጸጋ | ›› ›› ›› ›› | ከፍጡራን ሁሉ የበለጠ ጸጋ አላትና |
| አንቀጸ ብርሃን | ቅዱስ ያሬድ | በደጃፍ ይገቡበታል ይወጡበታል። ጌታም ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በድንግል ማሕፀን ቆይቶ ወጥቷልና |
| ማኅደረ መለኮት | ቅዱስ ያሬድ | መለኮትን በሥጋ ፀንሳ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይታለችና |
| መንጦላዕተ ብርሃን | ›› ›› ›› ›› | ብርሃን ጌታ በማሕፀኗ ዘጠኝ ወር ቆይቷልና |
| መንበረ ስብሐት | ›› ›› ›› ›› | በመንበረ ስብሐት እግዚአብሔር በዘፈቀደ እንደሚገለጥ በድንግል ግን በሥጋ ተገልጧልና |
| ርስት | አባ ሕርያቆስ | ከእርሷ ከተወለደው ጌታ ርስተ ሰማይ ተገኝቷልና |
| ሙኀዘ ፍሥሓ | ›› ›› ›› ›› | ፍሥሓ (ደስታ) የተባለ ጌታ ነው። |

| | | |
|---|---|---|
| የሸማኔ ጉድጓድ | ›› ›› ›› ›› | በሸማኔ ጉድጓድ ድርና ማግ አንድ እንደሚሆኑባት በድንግል ማሕፀንም ቃልና ሥጋ ተዋሕደዋልና። |
| ማዕዶት | ›› ›› ›› ›› | አበው ከሞት ወደ ሕይወት የተሸገሩባት ድልድይ |
| አዳም የታደሰባት | ›› ›› ›› ›› | ባሕርየ አዳም ታድሶ የተገኘባት ስለሆነች |
| የአዳም ተስፋው | ›› ›› ›› ›› | ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ተብሏልና |
| የአቤል የውሃት | ዘፍ.4፥8 | የቃኤልን ጠላትነቱን እያወቀ ተከትሎታልና |
| የሴት ደግነቱ | አባ ሕርያቆስ | ሴት አዳምን በቅንነት አገልግሎታል |
| የሄኖክ መልካም ሥራ | ዘፍ.5፥22 | እግዚአብሔርን በመውደዱ ተሠውሯልና |
| የሴም ምርቃት | ዘፍ.9፥27 | እግዚአብሔር በሴም ቤት ይደር ተብሏልና |
| የአብርሃም እንግድነት | ዘፍ.12፥20፣ ዘፍ.20፥14 | አብርሃም ወደ አቤሜሌክና ወደ ፈርዖን ሲሔድ ሞገስ ማግኘቱ ጌታ፣ ድንግል ማርያም በባሕርዩ ስለነበሩ ነው |
| የይስሐቅ መዓዛ | ዘፍ.22፥9 | በመታዘዙ መሥዋዕቱ ተወዷልና |
| የአሚናዳብ ሠረገላ | አባ ሕርያቆስ | ይቺ ልዝብ፣ ፈጣን እንደሆነች ድንግል ማርያምም በንጽሕና በቅድስና የለዘበች ናትና። |
| የሰሎሞን ቀለበት | አባ ሕርያቆስ | ሐሩራኤል፣ ጭርዋቅ የሚል ስመ አምላክ የተጻፈባት ናት። የሰሎሞን መንግሥት በቀለበት እንደተመለሰ የአዳም ልጅነት በድንግል ማርያም ልጅ ተመልሷልና |
| የሲሎንዲስ ዕፀ ሕይወት | አባ ሕርያቆስ | የሚያድንባት ዕፅ ናት። ጌታም ከድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን አድኗልና። |
| ዕጣን | ሥርዓተ ቅዳሴ | መዓዛ የክርስቶስ ምሳሌ |
| ገነት | - | በገነት ኃጢአት ርስት እንደሌለው ሁሉ ድንግል ማርያምም በኀልዮ፣ በነቢብ፣ በገቢር ንጽሕት ስለሆነች በገነት ትመሰላለች |
| ሐዳስዩ ጣዕዋ | ይዌድስዋ… | የሰባ መሥዋዕት የሆነ ክርስቶስን ወልዳልናለችና |
| በትረ ሃይማኖት ዘኢትጸንን | ውዳሴ ማርያም | በትር ከዕፀዋት ተለይታ ቀጥ ያለች እንደሆነች ድንግል ማርያምም ከሰው ሁሉ ተለይታ ጽነት የሌለባት በመሆኗ በትር ትባላለች |

## አምስቱ የድንግል ማርያም ኀዘናት

- ስምዖን ትንቢት በተናገረ ጊዜ (ሉቃ.2፥34)።
- ጌታን በቤተ መቅደስ ባጣችው ጊዜ (ሉቃ.2፥45)
- ጌታ በተሰቀለ ጊዜ (ማር.15፥27)
- ጌታን ሲቀብሩት (ዮሐ.19፥42)
- የጌታን እጁን አስረው ሲገርፉት (ዮሐ.19፥1)

## ክብረ ድንግል ማርያም

ድንግል ማርያም ጌታን ስለወለደችልን የጸጋ ምስጋናን እናመሰግናታለን (መዝ.33፥1)። የጸጋ ስግደትን እንሰግድላታለን (ሉቃ.1፥44)። በተሰጣት የማማለድ ጸጋ ታማልድልን ዘንድ አማልጅን

እንላታለን (መዝ.33፥15፣ ዘፍ.20፥1-7፣ ዮሐ.2፥1-5፣ ሉቃ.1፥20፣ መዝ.44፥9)፡፡ ሠላሳ ሦስቱን በዓላቷንም እናከብራለን፡፡ እነዚህም በየወሩ በ21 በ21 በ12 ወር 12 ይሆናል፡፡ መስከረም 10፣ ህዳር 6፣ ታኅሣሥ 3፣ ታኅሣሥ 22፣ የካቲት 16፣ ግንቦት 22፣ ግንቦት 23፣ ግንቦት 24፣ ግንቦት 25፣ ሰኔ 8፣ ነሐሴ 7፣ ነሐሴ 16 ናቸው፡፡ ታኅሣሥ 3 በሦስት ዓመቷ ወደ መቅደስ የገባችበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የስደቷን መታሰቢያ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 5 በማሕሌት ታከብራለች፡፡ ኤፍሬም ውዳሴዋን፣ ሕርያቆስ ቅዳሴዋን፣ ያሬድ አንቀጸ ብርሃንን፣ አባ ጊዮርጊስ አርጋኖንን፣ አባ ጽጌ ድንግል ማሕሌቷን፣ ደቅስዮስ ተአምሯን ጽፏል፡፡